አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፬

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

forth year No.34
ADDIS ABABA 9th days of July, 2012


**ማውጫ**

**የአዲስ አበባ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት አዋጅ**

**CONTENT**

**The Addis Ababa City Council office Proclamation**

### አዋጅ ቁጥር ፴፬/፪ሺህ፬

### የአዲስ አበባ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በከተማው አስተዳደር ቻርተር የተሰጠውን ሥልጣንናተግባር በአግባቡ እንዲያከናውንና ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማስቻል በማስፈለጉ፤

የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት በተሻሻለው የከተማው አሰተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩ /፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፲፬ (፪) (ሠ) መሠረት ህጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ በህግ ማቋቋም በማስፈለጉ ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም. አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና (፪) (ሠ) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### Proclamation No.34/2012

### The Secretariat of Addis Ababa City Council Establishment Proclamation

WHEREAS, it is found necessary to enable the City Council of Addis Ababa to perform the duties and responsibilities enshrined under the Revised Chute of the City;

WHEREAS, it is found necessary to establish the Secretariat of the City Council as an organ having juridical personality in accordance with the Revised Charter Proclamation No 361/2003 Article 14(2)(e) of the City Government;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-Article 1 and 2(e) of Article 14 of the Revised Charter Proclamation No 361/2003 of Addis Ababa the City Council has issued this Proclamation as follows;

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፬/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትረጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. ቻርተር ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩ /፲፱፻፺፭ ነው።

፪. "ምክር ቤት" ማለት በቻርተሩ አንቀጽ ፲፪ መሰረት የተቋቋመ የከተማው ምክር ቤት ነው፣

፫. "አፈ ጉባዔ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ነው፣

፬. "ጽሕፈት ቤት" ኃላፊ ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሰረት የተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ነው፣

፭. "የጽሕፈት ቤት ኃላፊ" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋመዉ የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ነዉ፡፡

**፫. መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሕጋዊ ሰውነት ያለው አከል ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል፣

፪. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አደረጃጀት ፣ ስልጣንና ተግባር

፩. የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት የጽህፈት ቤት ኃላፊ አስፈላጊ የሆኑ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፣

## Part one
## General Provisions

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Secretariat of Addis Ababa City Establishment Proclamation No.34/2012."

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise Proclamation:

1. **"Charter"** means the Addis Ababa city Government Revised Charter Proclamation 361/2003;
2. **"Council"** means the City Council established Pursuant to Article 12 of the Revised Charter.
3. **"Speaker"** means Speaker of the City Council Addis Ababa ;
4. **"Secretariat"** means the Secretariat of the Addis Ababa City Council established pursuant Article 3 of the Proclamation;
5. **"Head of the Secretariat"** means Head Secretariat of the Council established to this Proclamation.

**3. Establishment**

1. The Secretariat of the City Council of Addis Ababa (hereinafter called the "Secretariat) hereby established as an organ having legal personality;
2. The Secretariat shall be accountable to the Council.

## Part Two
## Organizational Structure Powers and Functions

**4. Structure and organization of the Secretarial**

1. The Secretarial of the Council shall have the Secretariat, the necessary work unit and

፪ የጽህፈት ቤቱ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በከተማ አሰተዳደሩ የመንግሰት ሠራተኞች ህግ መሰረት የሚተዳደሩ ይሆናል፡፡

**፭. የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.በምክር ቤቱና ምክር ቤቱ ለሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎችና ውስጣዊ አካላት አጠቃላይ አሰተዳደራዊ ግልጋሎት ይሰጣል፡

፪. ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች የሚያስፈልጉትን የመሰብሰቢያ አዳራሾች ያደራጃል፤

፫. የምክር ቤቱ ቃለ ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፬.ለምክር ቤቱ አካላትና አባላት የቤተመጻሕፍት፣ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤

፭. ምክር ቤቱ ያፀደቃቸውን ህጎች በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ እንዲታተም ያደረጋል፣ የምክር ቤቱን መጽሔቶችና ጋዜጦች ሕትመትና ሥርጭት ይከታተላል፤

፮.የምክር ቤቱ እንግዶች አስፈላጊውን የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረጋል፣
፯.የንብረት ባለቤት ይሆናል ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፰. የምክር ቤቱን አካላትና አባሎች ሥራ ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፮.የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባራት**

የጽሕፈጽ ቤቱ ኃላፊ አፈ-ጉባኤው በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የሚመደብ ወይም የሚቀጠር፣ ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት በአፈ-ጉባኤው በሚሰጠው አመራር መሰረት ሥራ ላይ ያውላል፣

2. The experts and other staff of the secretariat be administered in accordance with the service laws of the City.

5. **Powers and Functions of the Secretariat**

The Secretarial shall have the following power and functions:-

1. Render general administrative services to Council, its committees and other internal organ same;
2. Arrange meeting hails required for the general assemblies of the Council and its various committees;
3. Cause that the minutes and documents of the “Council are recorded and kept properly;
4. Provide library, research and information services to the organs and member of the Council;
5. Cause that laws adopted by the Council published in the Addis Negari Gazeta and follow the publication and circulation of laws, periodical and newsletters issued by the Council;
6. Cause the services of Cordial reception to extended to visitors of the Council;
7. Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;
8. Perform such other duties as are conductive to fulfillment of the activities of the organs members of the Council.

**6. Powers and Functions of Head of the Secretariat**

The Head of the Secretariat, who shall be employed or deployed based on the criteria stipulated by Speaker and is accountable to same, shall haw following powers and functions:-

1. Exercise the powers and duties of the secretariat specified under Article 5 of this Proclamation the order of the Speaker;

፪. የጽህፈት ቤቱን የሰራተኞች አሰተዳደር፣ እድገት፣ ቅጥርና ስንበት አፈጻጸም በከተማው የመንግስት ሰራተኞች ህግ መሰረት በማከናወን ለአፈጉባኤው አቅርቦ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፫. የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀትና በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ለምክር ቤቱ ቀርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፤ ሥራ ላይ ያውላል፣

፬. በምክር ቤቱ በፀደቀው በጀት መሰረት አፈ-ጉባኤው በሚሰጠው አመራር መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ ለታለመለት ተግበር ያውላል፣

፭. የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ለምክር ቤቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

፮. የጽሕፈት ቤቱን ንብረት በከተማው የንብረት አሰተዳደር ህግ መሰረት ያሰተዳድራል፣

፯. በአፈ-ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፯.በጀት

የጽሕፈት ቤቱ የበጀት ምንጭ፡-

፩. በከተማው አሰተዳደር ከሚመደብ በጀት፣

፪. እንዲሁም ከሌሎች ህጋዊ ገቢ ምንጮች ይሆናል፡፡

### ፰.የሂሳብ መዛግብት

፩. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክለለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

፪. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፣

2. Perform and submit for approval administration, promotion employment Dismissal; of employees of the Secretariat due regard to the civil servant laws of city effect the same up on approval;

3. Prepare the annual budget and work program to the Secretariat; submit same to the council through the Speaker for approval, and implementation same upon approval;

4. Effect expenditure in accordance with approved budget of the Council based on order of the Speaker utilize same for the intended program of the Secretariat;

5. Prepare reports on the activates and financial accounts of the Secretarial and cause the presented to the Council through the Speake;

6. Administer property of the Secretariat in accordance with property administration law of the City;

7. Perform such other activities as are assigned to him by the Speaker.

## Part Three
## Miscellaneous Provisions

### 7. Budget

The budget source of the Secretariat shall be from:-

1. Budget assigned to it by the City Government; and
2. Other legal revenue source.

### 8. Books of Accounts

1. The Secretariat shall keep complete and accountable books of accounts;

2. Books of accounts and financial dements Secretarial shall be audited by the Auditor General of the City animally.

፫. ሆኖም ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ በማናቸውም አስፈላጊ ጊዜና ሰዓት የሂሳብ መዛግብት ሰነዶች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ በዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ሊያዝ ይችላል፡፡

**፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ አፈ-ጉባዔ ጽህፈት ቤት ስም ሲያከናውኑ የነበሩ ህጋዊ ተግባራት በሙሉ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ተሸጋግረዋል፡፡

**፲ አዋጁን ስለማሻሻል**

ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን አዋጅ ሊያሻሽል ይችላል፣

፲፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩. የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪. የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጣ ደንብን ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪. አዋጁ በሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሐምሌ ፫ ፪ሺ፬ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.**

**ኩማ ደመቅሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

3. Without prejudice to sub article 2 of this Article the Speaker of the Council may order books of accounts and documents the whole or partially audited any time it deems necessary.

**9. Transitory Provisions**

All legal activities that were being undertaken by the Addis Ababa City office of the Speaker of Council shall be transferred to the Secretariat o Addis Ababa City Council

**10. Amendment of the proclamation**

The Council may amend this proclamation, when finds necessary.

**11. Power to Issue Regulation and Directive**

1. The Addis Ababa City Council may I regulation for the implementation of this proclamation;
2. The secretarial of the Addis Ababa City Co may "issue directive necessary for the implementation of the Proclamation or Regulation to be issued for the implementation thereof.

**12. Effects Date**

This Proclamation shall enter into force as of the 10th day of July, 2012.

**Date at Addis Ababa**
**This 9th day of July 2012**
**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**